# በራሴ ዕይታ--የቶሮንቶ ስብሰባ

*በራሴ ዕይታ እንዲሁም በእምነቴ*
*መጓዝ ከተሳነኝ እስከ ዕለተ ሞቴ*
*ተመሽልቆ ይጣል ኢትዮጵያዊነቴ።*

ከላይ ርዕስ ላደረግኩትና ወደ ታች ላሰፈርኩት የኃሳቤን ተዓማኒነትን ለመግለፅ ነው ስንኟን የቋጠርኳት ኢትዮጰያዊነቴን ምሰሶ ኢሕአፓነቴን ማገር አድርጌ በመንፈስ ቁስል የማልሰቃይ  በሀገር ፍቅር የምነድ ኢሕአፓነትን ከአያት ከአባት ያገኘሁ እስኪመስለኝ ድረስ ከምሬ የምመካበት፣ ከአዳጊነት እስከ ጉልምስናዬ ከኢሕአፓ ውጪ ባለመሆኔ የተሰዉ ጓዶቼን ዕርም ያልበላሁ ስለሚመስለኝ ሀብትና ፀጋ ጤናና ተስፋ የተሞላሁ ነኝ።

ስለራሴ ብዙ ካልኩኝ ወዲያ የዕለተ ሰንበት የቶሮንቶ ውሎዬን የምገልፀው ካሰፈርኩት እኔነቴ የመነጨ እንደሆነ አንባቢ እንዲረዳልኝ እፈልጋለሁ። እኛ ለእኛ የሚለውን ዕንሰ ሀሳብ እኔ እኔ የሚለው ጉልድፍ ዕምነት የሚፃረረው መሆኑን ከተረዳሁ ዘመን ያለፈኝ ቢሆንም ለዛሬዋ ፅሁፌ እኔ እኔ ብል እንዳትታዘቡኝ አደራ እላለሁ። በራሴ ዕይታ ነው የማቀርበውና።

ካለሁበት በብዙ መቶ ማይል ርቀት ወደምትገኘው ካናዳ ጉዞ የጀመርኩት አንድ ዓይኔ ብሌን ከምሳሳላቸው ጓዶቼ እናተ ዓለም ጠኑ (ማዘር) ጭምር በመሆኑ እንኳን 12 ሰዓታት 12 ደቂቃም የተጓዝኩ ሳይመስለኝ ነበር በምሽት ከቶሮንቶ ጓዶቻችን ጋር የተደባላቅነው። በጓዳዊ ፍቅር የተለወሡ ራታችንን አብልተው ወደ ተዘጋጀልን ማረፊያ የጓደ ቤት በመደዳ ተነጥፎልን ነበር እያወጋን ወደ ትንሹ ሞት እንቅልፍ  የተጓዝነው። ዕለተ ሰንበት በረፋዱ ተነስተን በወረፋ ተለቃልቀን የተዘጋጀልንን ቁርስ ከቆረስን በኋላ ለጉዞዓችን መንስዔ ወደ ሆነው የስብሰባ አዳራሽ ተከታትለን ሄድን።

አንባቢ እንዳትሰለቹኝ

12 ሰዓት ጉዞ ለአንድ ስብሰባ ለምን አስፈለገ  የሚል ጥያቄ ከመጣ መልስ ይሆን ዘንድ ትንሽ ልበላችሁ። ወርሀ ጥቅምት 2000 በደም የተገነባውን ታሪካዊ ጎጆ በዕምነትና ፍቅር የተሳሰረውን ፓርቲያቸውን በተሳሳተ ስሌት/ሂሳብ እናፈርሳለን ብለው ከፈጣኑ የጉዞ ባቡር ራሳቸውን የከሰከሱ ምስኪኖች የአናሳው ብዙሀኖች ቶሮንቶ በመሆናቸው ገጥ ለገጥ ለመተያየት ነበር ጉዞአችን። ሁለተኛው፣ ከአንጀኝነት ባህርያት አንዱ ነጩን ከቀይ ቀዩን ከነጭ ደርቶና ነርቶ ማቅረብ ስለሆነ በአደባባይ ቀደዳ ከጀመሩ በዓይን እማኝነት

የተመለከትነውን ዕብጠትና ፍንዳታቸውን ለመሟገትም ጭምር ነበር ወደ ካናዳ ያቀናነው:: ስብሰባው የተጠራው በቶሮንቶ ፀንቶ ዘለቅ ኢሕአፓዎች ነበር:: ሰዓቱም ከቀኑ 2 ፒኤም የክብር እንግዳ 35 ዓመቱን ቀጥ ብለው ተጉዘው 36ኛውን ከጀመሩት አንዱ የኢሕአፓ አዛውንት ጓድ ተገኜ ሞገስ ነበሩ:: ስል ኢትዮጵያ ዕጣ ፈንታ ለቶሮንቶ ኢትዮጵያውያኖች ገለፃ ለማድረግ ፤ ሃሳብ ለመቀበል ለመሞከር ጭምር::

የፀረ ኢሕአፓዎች አላስፈለጊ ቅስቀሳና፤ እየዞሩ ማስታወቂያ ቀደዳውን ጭምር ተቋቁመው ስለ ሀገራቸው መፃዒ ዕድል ለመምከር የመጡ ኢትዮጵያውያኖች የተዘጋጀውን ወንበር የሞሉት 3 ፒኤም ላይ ነበር:: ውሸት ምሱ የሆነ አንድ ተራ አንጃ (እግረኛ) በፓልቶክ 30 አይሞሉም እንዳለው ሳይሆን በ3 አባዝቼ 90 ይሆናል ስል በጥቅምቱ አብዮተ ራሳቸውን ያቀጠሉትን 4ቱን ጭምር መሆኑን ይታወቅልኝ:: መቼስ ይታገሉታል እንጂ ይታደሉታል አይደለምና በሰሩት ስህተት የተነሳ የውስጣቸው ፀፀት ከፊታቸው የሚነበበውን የትላንት ጓዶቼን የዛሬ ጉዶቼን ሰብሰባው ከተጀመረ በኋላ ያ ሁሉ የስብሰባ ታዳሚ ዓይን እየገረፋቸው መስረዕ ሰርተው ሲገቡ ሣያቸው እኔ ለነሡ ሃፍረት ያዘኝ:: ትላንት በፍቅር የተተበተብን ነበርንና፤ መተብተቢያውን የበጠሱትን የአዋቂ አጥፊ ረገምኩኝ:: በተለይ ከአራቱ በደምብ በጓዳዊ ፍቅር አውቃቸው የነበሩት ሁለቱ ጋር ተደርበውና ታጀበው ስመለከታቸው ሰወ በገዛ እጁ ማዕረጉን ይገፋል እንዴ????ነው ያልኩት:: ሁለቱ አንዱ የዱሮ ኢሕአፓ አንዱን እንጃ ከተናጋሪው ፊት ለፊት ካለው የመጀመሪያ መደዳ ወንበር ላይ ተቀመጡ:: ሌሎቹ አንዱ ከቀኝ አንዱ ከግራ ከኋላ ወንበር ላይ ተቀመጡ:: ስብሰባው እንደቀጠለ ነው::

የኢሕአፓ ተወካይ አቶ ተገኜ ሞገስ በተሠጣቸው ርዕስ ላይ አተኩረው ኢትዮጵያን እንደ ነቀርሳ እየበላና እየጨረሳት ስላለው ስንክሳር በርቱዕ አንደበታቸው ዘርዝረው ከጨረሱ በኋላ ወደ ጥያቄና መልስ ከመኬዱ በፊት ሐዋርያው ሙሉ ቀን እናት አሰለፈችን ለታዳሚው ዘረዘራት.. ያች 11 ልጆቿን ትታ ለሚሊዮኖች ስትል 35 ዓመት በጫካና በከተማ እስካሁን ትግል ላይ ያለች እኛ ሽዋረገድን ታሪኳን በአጭር ሲነገር ልቅሶ በተደባለቅ ኢትዮጵያዊ ስሜት ሕዝቡ ተነስቶ ከበሬታውን ለገሣት:: በዚህ አጋጣሚ አሻራ እናታችን ሰላኮራሽን ዕድሜ ይስጥሽ፤ የሀገርሽን ነፃነት ያሳይሽ ሳልላት አላልፍም:: በነገራችን ላይ ሁሉም የቤቱ ታዳሚ ተነስቶ በፍቅር ሲያከብራት ትላንት ማዘርዬ ሲላት የነበረው ከፊት የተቀመጠው አግሩን አጣምሮ ተቀምጦ ሣየው እኛነታችንን የሚገለፀው ለሰው ወይስ ለዕውነት ወይ መዓልቲ ብዬ ዘልየዋለሁ:: የማዘርን ዕውነታ በያነዳንዳችን ህዋሳት ንዝረትን ፈጥሮ፤ አስክኖ፤ አስቆ፤ ቁም ነገርን አስጨብጦ፤ ኢሕአፓ ማለት እናት መሆኑን ላላወቀ አሳውቆ በጭብጨባ እንደተነሳች በጋለ ጭብጨባና ከበሬታ ወደ ቦታዋ ተመለሰችና ሊቀመንበር ሐዋርያው በመርሀ ግብሩ መሰረተ ወደ ጥያቄና መልሰ አሸጋገረን::

ክፍል ሁለት

የመጀመሪያውን የጥያቄ ዕድል ካገኙት አንዱ በፍፁም የኢሕአፓነት እንጥፍጣፌ የሌለው፤ የባለታሪክ ባለቤትነት የማይጋራ፤ ኢሕአፓ እንደ ኩይሳ ቢፈራርስ ደስታ የሚሠጠው፤ ለጓዶቹ በተለይ ለፀንቶ ዘለቁ ክፍል ምቀኝነት የሚያጠቃው፤የእፊቱ ገፅታ ላይ የ ፀሃንን ደም የሚያጣጥም ጋኔል የሠፈረበት የሚመስለወው፤ ሚከሪና ወይ ጠበል ወሳጅ ያጣው አክሊሉ የተባለው ነበር፡፡ በነገራችን ላይ ከግለሰቡ ጋር ዕወቀትም ፍጥረትም የለኝም፡፡ ነገር ግን ይኸው ሰፌ ቤታችን ኢሕአፓ ነበረ ያገናኘን፡፡ እስካሁን ድረስ ምን እንደዚህ እንደሚያደርገው? ምን እንደሚፈልግ? ምን እንደሚጠቀም? እሡን ከኢትዮጵያ ችግር በላይ ምን እንዳደረገው ጥያቄውን ለራሱ ሠጥቸዋለሁ፡፡

ሰለ ታላቋና ጥንታዊ ኢትዮጵያ መጥፋትና መዳን ውይይት ላይ ለጥያቄ ተነስቶ አቶ ተገኜ አስመራ ሄደው ነበርን? ብሎ ጠየቀ ፡፡ አዎ ቢሉት ምን ሊሆን ነበር? አቶ ተገኜ ለኢትዮጵያ የነፃነት ትግል ይጠቅማል ተብሎ ድርጅታች ከወሠነ ለምን ሙሦሊኒን ከመቃብሩ አውጥተው አይ/ነጋገሩም? ጥሎ ከወጣ በኋላ ምን ያገባዋል? ምን ያንጨረጭረዋል? ኢሕአፓ አንኳን <u>በአሉባልታ፤ በደርግ፤በወያኔ በሻዕቢያ ባባዕዳን ሴራና ዱላ</u> ስላልጠፋ በከንቱ አትልፋ! እለዋለሁ፡፡ አቶ ተገኜን አፋጠጥኩ ለሚል ምርቃና ከሆነ ጎሽ ወንዳታ የሚልህ መሪ ካለህ ገልገሊቲ ቶላ እንቀቡ ብዬህ እዘልሃለሁ፡፡ በሠራኸው ፀፀት የሚሠማው ፍጡር ከሆንክም መሃሪ ድርጅትህን ይቅርታ ጠይቀውና ተደባለቅ--ደግመህ ካልከዳህ እንደ ዶክተር እንቶኔ!

ሌላው ጠያቂ-- ከልጅነቱ ጀምሮ እስከ አለፈው እሁድ በሰብሰባ ተናግሮ ሃሳቡ ተቀባይነት ካጣ ወጣ ማለት የለመደበት ዪያኔ ጓዳችን የዛሬ አንጃችን መስፍን መድኃኔ ነበር፡፡ ያለ አጀንዳ አታውራ ብሎ ቤቱ ሲያጉረመርም (ሲጮህበት) ካልፈለጋችሁ እወጣለሁ ሲል "እንደገና!" ያሉት አልጠፉም፡፡ ለመሆኑ ይህ ሰው ወጥቶ ወጥቶ አያልቅም እንዴ ሚል የሰማሁትም አልታጣም፡፡ ከሜዳ በወጣትነቱ መሄድ፤ ከ 4ኛው ጉባዔ ሃሳቡ አራት ደጋፊ ብቻ አግኝቶ ሲሸነፍ መሄድ፤ መዉጣት፤ በልዩ ጉባዔ ጥሎ መሄድ፤ ዛሬ ደግሞ በህዝብ ስብሰባ ካልሰማችሁኝ እሄዳለሁ በማለቱ ነው መስፍን መድኃኔ የሚለው ስሙ ተቀይሮ መስፍን መሄዴ የሚል ሰም በዚያው ቀን የወጣለት፡፡ ስብሰባው ከዚያ በኋላ ኮሽ ሳይል ግቡን መትቶ፤አንጃው ሚዛን እንደማያነሳ ህብረተሰቡ ተረድቷል፡፡ ይልቅ ማረኝ ድርጅቴ ብላችሁ ሃዲድ መሳት እንዳለ ወደ ሃዲድ መመለስም በኢሕአፓ ታሪክ ያለ በመሆኑ የራሳቸሁን ዝናና ክብርን ከኢሕአፓ ብሎም ከኢትዮጵያ ያስበለጣችሁ ካልሆናችሁ፤ ባዕድ ጥላውን ካልጣለባችሁ <u>በራስ ዕይታ</u> የድሮ ጓዶቼ ነበራችሁና ጥርሱ ለረገፈ አብዮት ጥበቃና ካድሬ መሳቂያ ባትሆኑ እመርጣለሁ፡፡ ጠቅላላ በኢሕአፓ ታሪክ ያለፈና አሁንም በትግል

የቀጠለውን ጭምር እናት አባቶቻችንን ጭምር በህይወት ያሉት ደርገና መኢሶን፤አብዮት ጥበቃና ካድሬ ከሚለው መጠሪያ በበለጠ ሠፊ አካለታችንን የሚነዝረው አንጃ የሚለው ጉድ መሆኑን ስነግራችሁ በዓየ  ህሊናዬ የሚመላለሰውን የጓዶቼን የደም ጎርፍ በማስታወስ ነው፡ በራሴ ዕይታ  ይህን ካልኩኝ ስብባው የታቀደለትን ድል ተጎናፅፏል፡፡ የአንጃው ምሽግ ፈርሷል ስል ለራስ ዕርካታ ብቻ ሳይሆን የ 240 ሺ ሠማዕቶችንም ማዕረግ ለመጠበቅ እንጂ...  ስብሰባው ካለቀ በኋላም ከ 45 በላይ ሀገር ወዳዶች ተሠባስበን ራት ተጋብዘን ኢትዮጵያዊ ትዝታችንን እንደያዝን ብዙ ወንድሞችና እህቶች ጋር ተዋውቀን፤የጋራ ጠላታችንን ለመጋፈጥ የመንፈስ ቁርኝት አበጅተን ተሰነባበትን፡፡ በዕኩለ ሌሊት ጉዞ ወደ መጣንበት ጉዞውን ተያያዝ ....

ይህ ነው የእኔ ዕይታ

## ከ ገዳ ውቤ

ኢሕአፓ እምዬ
የልጅነት ቤቴ
ካንቺ በፊት ያርገው
አይቀሬወን ሞቴ፡፡
እማዬ ልበልሽ በእናት አስመስዬ
አሳጥሬ ልጥራሽ እያልኩኝ አባዬ?
የኔ ፍቅር ብልሽስ
የኔ እምነት ብልሽስ
ልቤ ውሰጥ ያለውን
እሳት ስገልፅልሽ፡፡
ተስፋዬ ነሽ አንቺ
ፀጋዬ ነሽ አንቺ
እያልኩኝ ባዜምስ
ብሮክር ባቅራራ
ባለቤት ስለሆንኩ አንዳችም ሣልፈራ፡፡
ከናቴ ጡት ኋላ
ከጨቅላው ዘመኔ
አንቺን ነው ያገኘሁ

ወለላ ነሽ ለኔ::

ዶሴዬን ከፍቼ ያለፈ ዘመኔን

ሳገላብጣቸው

የልጅነትግዜ የተዋወቅኋቸው

መስዋዕት ጓዶቼን በሀሳብ ሣያቸው

ይብላኝ ለገዳዩ እነሱ ህያው ናቸው::

ገደላቸው እንጂ መች ደርግ አጠፋቸው::

ዕድሜ ላንጅ ይበል

ከፍቶ ላሥበላቸው::

ሽንቁጤ ሳህሌን

አህመዲ ሁሴን

ሙደሰር አስማንን

መሀመድ ሙዜይን

ሰብስቤ ሣህሌን

መስፍን ሀብታሙን

ሌሎችንም ጭምር

ትንታግ ኢሕአፓዎች

ዛሬ የሚጠሩኝ

ታገል ታገል ሚሉኝ

ብስሉ ጓዶቼ

ፅኑ ወንድሞቼ

አንጃ የፈጃችሁ

መልምሎ መልምሎ

ለደርግ ያስበላችሁ

ኤልያስ ፀጋዬ ክፉ ገዳያችሁ

እሱ ቆሞ ይሄዳል እናንተ ሞታችሁ::

እሱ ግን ይረግፋል እናንተ አብባችሁ::

ተክልዬ አደባባይ አንጃ ያቆሰለህ

አንገትክን አቅኝቼ ጓዴ አህመድ ስልህ

አባ አባ ስልህ

አንዴ ቀና ብለህ

ዓይኔ ዓይኔን እያየህ

ኢሕአፓ ዕውነት ነው

ቀጥል ቀጥል ብለህ

ተዘጋ  ትንፋሽህ ።

ይኼ ለእኔ ቃል ነው የዕምነት አደራ

እህትህ እግርህን

ሌላ አካላትህን

እኔ አዳጊውም ተሸክመን ይዘን

በትግል መሞት ህይወት

ባመፃ መሞት ህይወት

ዳግም ትንሳዔ ልደትን

ደግመን እየዘመርን

ታላቁ ጓዳችን አህመድን ቀበርን።

ደምህ ስለነካኝ ደም ስሬ ውስጥ ገብቶ

ያንቀሳቅሰኛል ዕምነት ብርሃን ሰጥቶ።

አንተን የገደለ

እምዬ ኢሕአፓን በጠላት ያስጠቃ

ማይመለስ መስሎኝ የዛኔ ያበቃ

ትግሌን አፋፍሜ

ፀጋዬ ደብተራን መባዕ ከፍዬ

ወረቃማ ጓዶቼን ደበዛ አስጠፍቼ

ዳገቱን ጨርሼ ብርሃን እየታየኝ

አፋፉ ላይ ስደርስ እያልኩኝ ቀን መጣ

ያ መናጢ አንጃ ደሞ እንደ አዲሱ ዴ ዴ ብሎ መጣ።

ጓዴ አህመዴ ባንጃ የተበላሽው

ሌሎችም ጓዶቼ ባንዳ የፈጃችሁ

መልዕክት ልንገራችሁ

አንጀኛ ሚባል ጉድ ሁለቴ ሊገለን መለስ ብሎ መጥቶ

በኢሕአፓ ጉባዔ ፍቅር መስሎ ገብቶ

በጠፍ በጨረቃ በድብቅ ፈርጥጦ

ዴ ዴ ብሎ ወጣ ውርደትን አንግቶ!!

ሰማዕት ጓዶቼ በጣም ምወዳችሁ

ሁሌም ጎኔ ቁሙ ፍርሀቴን ገድላችሁ!

ገዳ ውቤ